# የሚፈለገው አማራው ከድጥ ወደ ማጡ እንዲወርድ ነው

አብነት ሁነኛው

በቅርቡ ሰማያዊ ፓርቲና ግንቦት 7 ተዋህደዋል። ሰማያዊ ፓርቲና ብአዴን ደግሞ ባህርዳር ላይ በገዱ ቢሮ ተሰብስበው አንድ ለአማራ ሕዝብ ዝርዝሩ ያልተገለጸለት ስምምነት ተፈራርመዋል። አቶ ገዱ ከቅርብ ግዜ ትዝታችን እንደምናስታውሰው በፊርማቸው ግጨውንና አካባቢውን ከጠገዴ ወረዳ ቆርጠው አሳልፈው ለትግራይ ክልል በማስረከብ " በትግራይና አማራ ክልሎች መካከል የነበረውን የድንበር ችግር ለአንዴና መጨረሻ ፈትተነዋል።" ብለውናል፤ ለመሆኑ ከሰማያዊ ፓርቲ ጋር ሲፈራረሙ ምናችንን አሳልፈው ሰጥተውብን ይሆን? ጉዱና ጭራውን አንድ ቀን ግዜው ሲደርስ የምናውቀው ቢሆንም እዛው ድረስ አማራው ለተፈረጀበት የሚስጥር ተንኮል በዝምታ መጠበቅ የለበትም። ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ እንዳይሆንብንና አሁን አማራው ካለበት የመከራ ድጥ ወደ የማይወጣው ማጥ ውስጥ ከመግባቱ አስቀድሞ የራሱን እርምጃዎች መውሰድ ይጠበቅበታል።

1/ ሁላችንም እንደምናውቀው ኢሕአዴግ ባገር ውስጥና ካገር ውጪ ከሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ አሁን ተፎካካሪ ከተባሉ ድርጅቶች ጋር ' ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ' የሚባልና በ 2012 በሚደረግ ምርጫ እንዲሳተፉ በሩን ገርበብ አድርጎ ግቡ የሚል ዓይነት ስምምነት አደረኩኝ ብሎናል። ድርጅቶቹም የእንገባለን ድምጽ አሰምተዋል።

2/ ተቃዋሚ ነን ሲሉንና ወያኔያዊው ኢሕአዴግ ካልወደቀ ሰላም የለም እያሉ ለበርካታ ዓመቶች ቡራ(ጉራ) ከረዩ ሲነዙ የነበሩት አሁን ሰተት ብለው ወደ አዲስ አበባ በመግባት ላይ ናቸው። እዚህ ላይ ለምን ገቡ ብዬ ለመከራከር አልሻም። እያንዳንዱ ስብስብ የራሱን አቅም የመውሰድ መብት አለውና። በተጨማሪም እውነት ሰላም የሚገኝበትም ከሆነ ችግር የለብኝም። ግን ምን ይዞ ጉዞን ማጤን ችለውበት ይሆን? በበኩሌ እኔንጃ!

3/ ከነዚህ ቡድኖች መካከል አብዛኞቹ አማራን የሚጠሉ ስለመሆናቸው ግን ማንም በአማራነት የቁም ስቅሉን እንደቀመሰ ሰው አሁንም ቢሆን በሁሉም ላይ ሳይሆን በፀረ አማራዎቹ ላይ ጥርጣሬ አለኝ። ስለዚህም የተገፉ አማራ ሀሳቤን እንደሚጋራ አምናለሁ። ያልተገፉና ላለፉት 27 ዓመቶች ከወያኔ በሚወረወርላቸው ትርፍራፊ በተላላኪነት የሚያገለግሉ አማራዎች ደግሞ እንደሚቃወሙኝ አልጠራጠርም።

4/ በትክክል ወ/ሮ እማዋይሽ ባህርዳር ላይ መደመርን አስመልክተው " . . . የሽግግር መንግስት ልናቅቁም ነው፤ ወይንስ በተቀደደልን ቦይ ልንፈስ ነው? " ያሉት ዛሬ እውነታውን አውቀነዋል። ጠ/ሚኒስትር አብይ አህመድ በዩናይትድ ስቴትስ ቆይታቸው ፍንክች ሳይሉ " የሽግግር መንግስት አይቆቅምም። ሕገመንግስቱም አይሻሻልም። አገር ቤት ገብታችሁ በምርጫ ተወዳደሩና ኢሕአዴግን ለማሸነፍ በሰላምና ፍቅር ታገሉ።" አገር ቤት ለገቡና ለመግባት ለወሰኑት ድርጅቶች በማያሻማ ቅንቅ ነግረዋቸዋል። አለቀ ደቀቀ፤ ፓርቲያቸው እስከ 2012 ምርጫ ውጤት እስኪታወቅ ስልጣን ለማንም አያጋራም። ስልጣን ለመጋራት የሮጠው ሁሉ አመድ አፋሽ ሆነ ማለት ይሆን? በባዶ መደመር የዘመኑ ድንቅ የፖለቲካ ጥበብ ሳይሆን አይቀርም። ከኔ በላይ ላሳር ይሉን የነበሩትን ሁሉ አፈዘዛቸው፤አደነገዛቸው።

5/ ወደ አማራው ጉዳይ ልመለስና ይህ ማለት በመደመር ወቅትና ከዛም አስቀድሞ ከጠ/ሚኒስትሩ ጋር ባደረጋው ስብሰባ ላይ የተነሱት የሁመራ፤ወልቃይት፤ጠገዴ፤ጠለምት፤ራያና አላማጣ፤መተከል ጉዳዮች ለ 27 ዓመት ሙሉ በምናውቀው የጉልበተኞችና ቀማኞች እጅ ውስጥ መገዛታቸውንና በመሰረተ ልማትና በባጀት አናሳነትም አማራው

መወገሩን ይቀጥላል ማለት ነው። አማራው ተደመረም አልተደመረ ኢሕአዴግ ስልጣን ላይ እስካለ የቁም ስቅሉን ከማየት ውጪ መዳኛ የምትባል መድሀኒት አያገኝም። ዶሮን ሲያታልልዋት በመጫኛ ጣልዋት እንደሚባለው ብአዴን በነሀሴ ስብሰባው ለይስሙላ በአማራው የተጠሉትን አመራሮቹን በእድሜና በቤተሰብ ወዘተ. ሰበቦች በክብር ተሰናብተዋል የሚል ዜና እንደሚሰራና ውስጥ ውስጡን ግን በነዚሁ የአማራ ጠላቶች አመራር ውጪ ሊሆን የማይችል መተንፈሻ ሳንባ የሌለው ስብስብ እንደሆነ ታውቆ በ 2012 ምርጫ እንዲወድቅ ካሁኑ መስራት ያስፈልጋል። እርሱም የአማራውን ኅልውና ከሚያናጉ ሀይሎች ጋር ተዋውሎ እንደሚሰራ መታወቅ ይኖርበታል። ብአዴን አማራውን ለማጥፋት አይቦዝንም። ስለዚህ የአማራ ብሔረተኞችና የተጋድሎው አባሎችና ደጋፊዎች ይህን እኩይ ስብስብ ቅስሙን ለመስበር ከመንቀሳቀስ መቦዘን የለባችሁም።

6/ ከመላው ኢትዮጵያ በተለይም ከኦሮሚያና ቤኒሻንጉል የአማራው መፈናቀል አይቆምም። ምክንያቱም ከወሬ ባለፈ ዶ/ር አብይ በሚቆጣጠሩት ፓርላማ መፈናቀልን የሚያቆምንና አፈናቃዮችን በሕግ የሚያስጠይቅ ድንጋጌ አይመጣምና። ምክንያቱም አማራውን በማፈናቀልና ከአማራ የፅዱ ክልሎችን እውን የማድረግ ፖሊሲ ወያኔ ሕወሐት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ኢሕአዴግ በአባል ድርጅቶቹና አጋሮቹ በሚባሉት ለ 27 ዓመት ሙሉ በፌደራል ባጀትሲያስፈጽመው የኖረው ዓላማው ነውና። አብይ ወደ ስልጣን ከመጡ ወዲህ የአማራው መፈናቀል ብሶበት የለምን? በጎባ፤ቡኖበደሌ፤ሸዋ፤አሶሳና መተከል ስንቱ አማራ ተጨፍጭፎ ምን እልባት ተደረገለት? በራሱ አገር በጭልጋ እስከዛሬ በቅማንት ታጣቂዎች የሚፈናቀለውና የሚገደለውስ? በኦሮሞ ልዩ ዞን በከሚሴና በባቲ አማራው ላይ የደረሱ በደሎችስ? " ሀላፊዎች ተነስተዋል " ከሚል ድለላ ውጪ መደመር ለአማራው እስካሁን ምን ጥቅም አስገኝቶለታል? ያልታደለው አማራ ዛሬም በሱዳንና በትግራይ ታጣቂዎች ሰለባ ይሆን የለምን?

7/ ሙሉ አፈጣጠሩና አቅሙ የወያኔ ሕወሐት የሳንቲም ገጽታ የሆነውና በጭን ገረድነት የፋሽስት ትግሬዎችን ፀረ አማራ ማኒፌስቶ በተላላኪነትና ዘበኝነት የሚያስፈጽመው ብአዴን ' ትምክተኛ፤ለሆጫም፤ከባዶ እግር መሄድ ያልወጣ፤ነፍጠኛና አሸባሪ፤የብሔር፤ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጠላት' ወዘተ. ብሎ የፈረጀውን አማራ እንዲነቃም ሆነ ተደራጅቶ ኅልውናውን እንዲይስጠብቅ አይፈልግም። የድርጅቱ ማንነትና ውሎው ራሱ ከ 1983 ዓ/ም አንስቶ እስካሁን በአማራው ላይ በደረሱና በሚደርሱ በደሎች አንጻር ሲገመገም ቅንጣት ያህል አማራነትን ያልተላበሰ ገጽታ እንዳለው በሁለተኛ ዜግነት እየተወገረ ያለው አማራ በየስብሰባው አብይ ስልጣን ላይ ቁብ ካሉ ጀምሮ በአደባባይ እሮሮውን እያሰማ ለብአዴን " አትወክለንም፤ ከስልጣን ውረድልን፤ አታውቀንም፤ አናውቅህም፤" ወዘተ. ሲለው መክረሙን ተመልክተናል። እስካሁን ግን ብአዴን ስለደነቀረ የሚሰማና የሚስተካከል አይነት ቆራጥ እርምጃ ሲወስድ አይታይም። መሀል ሰፋሪነት የሚባል ደዌ ተጸናውቶት ይሆን? ለማንኛውም ድርጅቱ ቆምጨጭ ብሎ ራሱን በማጽዳት ውስጡ አሉ የሚባሉት የለውጥ አባሎች የሚቆጣጠሩት ከሆነና ዲሞክራሲያዊ ብሔረተኝነት የሚላትን የባዶ ማደናገሪያ በመወርወር የአማራን ብሔረተኛነትን አምኖ ከተቀበለ ከሞት መዳን ይችላል። እጁን ለአማራው ተጋድሎ አሳልፎ መስጠት ሽንፈትና ውርደት ሳይሆን ብልህነት መሆኑን ብአዴን ውስጥ ያሉ የአማራ ልጆች ማመን አለባቸው።

8/ በምዕራባዊያን ተፅዕኖ ውስጥ የተዘፈቀው ኢሕአዴግ የሁለት ዓመት ግዜ በቀረው ምርጫ ስልጣን ለተቃዋሚ ወይም በቅርቡ ተፎካካሪ ለተባሉት ድርጅቶች በፓርላማ ውስጥ ለይስሙላ ጥቂት ወንበሮችን በማካፈል ሆኖም ግን በሚወሰኑ ጉዳዮች ላይ ከመጮህ ሌላ ምንም ለውጥ ማምጣት የማያስችል ባዶ ስልጣን ለማጋራት የተስማማ ይመስላል። እንግዲህ ለተፎካካሪዎች ላም አለኝ በሰማይ ወተትዋንም አላይ ሊሆንባቸው ነው። ይህንን እያወቁ መደመርን የመረጡትና ተሰባብሮ ገደል ሊገባ አንዲት እርምጃ ብቻ የቀረውን ወያኔ የማዳናቸው ነገር እንቆቅልሽ የሆነብን ብዙ በደሎች የደረሰብንና የደረሰባቸው አማራዎች አለን። ሁኔታው ለብአዴን ሕጋዊ እውቅናን ጨምሮ በደንብ አድርጎ ብርታት የሰጠው ይመስላል። ምክንያቱም በአማራ ስም ተደራጅተው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ቡድኖች ዛሬ አዲስ አበባና ባህርዳር ላይ ከአመራሮቹ ጋር ንግግሮች መያዛቸውን ሰምተናልና። ለምን ገባችሁ ሳይሆን ምን

ለአማራው የሚጠቅም ቁም ነገር ይገኝበታል ነው የምትሉን ለማለት ፈልጌ ነው። ሰፋ ያለ ማብራሪያ ብትሰጡበት መልካም ይመስለኛል። በማስረጃ የምታሳምኑን ከሆነ ችግር የለም ለማመን እንችላለን። እንኩ እስክትሉን ድረስ ግን ጥርጣሬያችን ይቀጥላል።

9/ ባህርዳር ላይ በቅርቡ የሰሚያዊ ፓርቲ አመራሮችና ብአዴኖች በአቶ ገዱ መሪነት ተሰብስበው ስምምነት ስለ መድረሳቸው በአማራ ቲቪ ዜና ሆኖ ቢቀርብም የስምምነቱ ዝርዝር ግን ይፋ አልተደረገም። በተለይም ይሄ ነገር የሆነው አብን (የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ) በተመሰረተ ማግስት ስለነበር፤ የስምምነቱ አስፈላጊነት የአማራውን ብሔረተኛነት መጎልበት አዋኪቦ ባጭር ለመቅጨትና አብን በ 2012 ምርጫ ተሸንፎ በተሰፋ መቁረጥ እንዲጠፋ ለማድረግ አቅጣጫ ላይ ያተኮረ ይመስላል። ሰማያዊ ፓርቲ ደግሞ ከግንቦት 7 ጋር ስለተዋሀደ የተወሰኑ የፓርላማ መቀመጫዎችን በተመረጡ በተለይም ለሁለትና ሶስት ዓመቶች በአማራው ተጋድሎ ተወጥረው በነበሩ ቦታዎች ላይ ሰማያዊና ግንቦት 7 ን አሸናፊ አድርጎ ለማውጣት የተቀነባበረም ተንኮል ሊሆን ይችላል።

10/ ሰማያዊና ግንቦት 7 በአማራ ብሔረተኝነት የማያምኑና አስፈላጊነቱንም የሚኮንኑ ድርጅቶች ናቸው። ሁለቱ የፈጠሩት ጥምረት ካላቸው የገንዘብና የድርጅታዊ አሰራር ልምድና እሳት የተባለ የሚድያ ተቅም በፕሮፓጋንዳ የመደገፋቸውን ሀቅ መሰረት ተደርጎ ሲገመገም ገና በመዳህ ደረጃና በገንዘብ ላልጎለበተውና የሚዲያ ተቅም አልባ ለሆነው አብን ከኢሕአዴግ ግርጌ እነዚህ የአማራውን በማንነቱ እንዲደራጅ የማይፈልጉ ሀይሎች የመቆማቸው ነገር በቡሀ ላይ ቆረቆር እንደሚሆኑበት መገንዘብ አያዳግተንም። የሁኔታው አስጊነት ለመደመር በጋራና በተናጠል የወሰናችሁ አድማስን የመሰረታችሁ ከቤተ አማራ በስተቀር የተሸረበው ተንኮል ሊዳረሳችሁ እንደሚችል ሳትረዱት የሚቀር አይመስለኝም። ስለዚህ ተንኮሉን ለማምከን ምን ያህል ዝግጅት አላችሁ?

11/ እየጎለበተ የመጣውን የአማራ ብሔረተኝነትና የአማራው ወጣት በአደባባይ ብአዴንን ማጋለጡና መኮነኑ ለኢሕአዴግ አገዛዝ ችግር ስለሚሆን ገዢው ፓርቲ በብአዴን አማካኝነት የአማራውን ቅስም ለመስበር ባለው ሀይል ሁሉ ስለሚጠቀም አሁን ባለው ሁኔታ አማራው የጀመረውን የማንነት ማጎልበትና ብሔረተኛነት አለዝቦ መደመር ላይ ብቻ የሚረባረብ ከሆነ የአማራው ጎልውና ጠላቶቹ ከሚፈልጉት ማጥ ውስጥ ሊዘፈቅ ስለሚችል ብርቱና ቆራጥ ጥንቃቄ የሚያሻበት የታሪክ ወቅት ላይ እንዳለን አውቀን ለፋታ እንከዋን መዘናጋትና ለነሰማያዊና ግንቦት 7 ጎልውናችንን አሳልፈን መስጠት አይኖርብንም እላለሁ። እነዚህ ፓርቲዎች ለአማራው የመኖርና አለመኖር ትግል በአጥፊነታቸው መፈረጅና የአማራውን ወጣት እንዳይቆጣጠሩት ለማድረግ አብንና አድማስ አንድ የጋራ ህብረት በመፍጠር መታገል ያለባቸው ይመስለኛል። አብን ተመሰረተ ሲባል ሁሉም በአማራ ስም የተደራጁ ሀይሎች የድጋፍ መግለጫ ማውጣታቸውን ሳስታውስ አሁን ደግሞ ተባብረው አማራውን ለማዳን የሚያዳግታቸው መስሎ ስለማይታየኝ ወደ ትብብሩ ፈጥነው ቢያመሩ የሚያዋጣ የፖለቲካ አካሄድ እንደሆነ መታወቅ አለበት።

12/ አማራ የሆነ ሁሉ የሰሚያዊና ግንቦት 7 የስልጣን ጥማት ማርኪያ ከመሆን ራሱን መታደግ አለበት። እነዚህ ሁለት ቡድኖች ተረባርብርው አማራውን እንደሌጣ ፈረስ ያለ ኮርቻ ሊጋልቡት ከብአዴን ጋር የሸረቡት መርዝ በኦሮሚያ፤በትግራይ፤በኢትዮ ሶማሌ፤አፋር ምንም ዓይነት ቦታ እንደሌላቸው ስላረጋገጡ አማራን የሙጥኝ ብለው የፓርላማ ወንበር ለመያዝና የስልጣን ጥማቸውን ለማርካት እንጂ ለየዋሁ አማራ ተቆርቾሪ ስለሆኑ እንዳልሆነ ግንዛቤ መውሰድ ያስፈልጋል። ኦሮሞው በኦነግና በአምሳሉ በተፈጠሩት ጫጩቶች ዙሪያ የሙጥኝ ብሎ የሌላ ድርጅትን ላለመቀበል ወስኖ እንደተሰለፈው፤ ትግሬዎችም ወያኔ ወይም ሞት ብለው ገትረው እንደተሰለፉት አማራውም በአብንና አምሳያው በሆኑ ድርጅቶች ላይ ብቻ እምነቱን በመጣል ማንነቱን ማጎልበትና ከጥፋት ራሱን ማዳን ይጠበቅበታል። ኢትዮጵያዊ ይሉንታውን መስበር አለበት። ኢትዮጵያን የሚያድነት የመላው አገሪቱ ሕዝብ አንድ ላይ ሲቆም እንጂ አማራው ብቻውን ጭዳ እየሆነ ሊያኖራት እንደማይችል እርግጠኛ የሆነ ግንዛቤ ሊኖር ይገባል። አዎ! ኢትዮጵያን በቁንጮነት ደሙን አፍስሶ አጥንቱን ከስክሶ አማራው እዚህ ደርሶዋል። በ 27 ዓመት

ውስጥ የሆነውንም አይተነዋል። ዘጎቻችን፤ወንድምና እህቶቻችን በምንላቸው በወተር፤አርባጉጉ፤በጉራፈርዳ፤ በመተከል፤በጊምቢ፤በመዠንገር፤በወልቃይት፤በጅማ፤በጎባ፤በኦጋዴን፤በአፋር፤ ወዘተ. በአማራነታችን ተነጥለን ደማችን በግፍ ፈስዋል። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የአማራውን ነፍስ ያልበላ አንድም ጎሳ የለም። ለ 600 ዓመት አብረን አገራችንን፤ሀብታችንን፤ፍቅራችንን፤ገበናችንን አካፍለንና አቅፈነው የኖረው ቅማንት ሳይቀር ጠላት አድርጎን አገሩ የኔ እንጂ የአማራ አይደለም ብሎ እየጨፈጨፈና እያፈናቀለን አይደለምን ያለው? አማራ ሆይ! አትዘናጋ! የቀን ጅቦች ሊበሉህ የመጨረሻዋ ምእራፍ ላይ ደርሰዋል። በራስህ ማንነት ኮርተህ ቁም!!! ኢትዮጵያ የጋራ ቤታችን እንጂ የግላችን አይደለችም።

13/ የኢትዮጵያ ሶማሌ መሪዎች ለ 27 ዓመት ከወያኔ ጋር የነበራቸውን እፍፍ ያለ ፍቅር አሽቀንጥረው በመጣል በአደባባይ ከሕወሐት ጋር ፍቺ ፈጽመዋል። ከጊዜው ጋር አብሮ መራመድ ማለት በራስ ሳንባ መተንፈስ ስለሆነ ኦጋዴኖች በቆራጥነት መቆም መቻላቸው በመንታ ምላስ " አብይን ስልጣን ላይ ለማምጣት ወሳኝ ሚና ነበረኝ " እያለ ዞር ብሎ ደግሞ " ሕወሐት ተጠያቂ የሚሆነው በትግራይ ብቻ ነው፤ እኛ ዘንድ ባለው ችግር እጁ የለበትም ነጻ ነው" በሚል ማላዘን ለተጠመደውና አማራዎች ሲፈናቀሉና ሲገደሉ ጆሮ ዳባ ልበስ እያለ ሲኖር ጃዊ ላይ ትግሬዎች ተገደሉ በሚል የነደብረጽዮን ቃለአጋኖ የሆነው ብአዴን ት/ት ሊወስድ ይገባዋል። አለበለዚያ ራሱን እያጠፋው እንደሆነ ማወቅ ይኖርብርታል። በተደጋጋሚ እንዳሳሰብኩት ብአዴን ራሱን ለውጦ ከአማራው ጎን እንዲሰለፍ ከየአቅጣጫው የሚቀርብለትን ጉትጎታ ከመቀበል ውጪ ሌላ አማራጭ ስለሌለው ከሕወሐት ጋር መፋታት ይኖርበታል የሚል እምነት በአማራው በኩል ተፈጥሮዋል። ብአዴንን አክርረን የምንወቅሰው አማራ እንዲሆንልን ስለምንፈልግና በጎጥ፤ በቀበሌ፤ በከተማ፤ በወረዳ፤ በዞንና በክልል የዘረጋቸውን መዋቅሩን በሙሉ የአማራውን ኅልውና ለማዳን በሚደረገው ትንቅንቅ በአጋርነት ከተጨኞቹ አማራ ሕዝብ ጎን እንዲሰለፍ ስለምንሻ ብቻ ነው። ውስጡ ያሉ አማራዎች ትላንትም፤ ዛሬም፤ ነገም ወንድምና እህቶቻችን ናቸው። ይቅር ለፈጣሪያችን እግዚአብሔር ተባብለን መታረቅ እንችላለን። አብረን በመሆን አማራን ከፋሺስት ወያኔዎች ሰላባ እናድነው። አብነት ሁነኛው ነኝ!